

ሌላው አስተያየት...

ሰዎች በተፈጥሮና በአካል እንደሚለያዩት ሁሉ በአመለካከታቸው፣ በአስተያየታቸውና በአቀራረባቸው ይለያያሉ። አንድ ሰው እንደተሳሳተ ካወቅክ ምከረው። ስህተቱን ልታርምለት ሞክር። የማያዳምጥህ ከሆነ እንደ አንዱ ጠላትህ አድርገህ አትመዝግበው። ነገሮችን በበጎ መልኩ ተመልከታቸው።

አንድ ጓደኛህን ልታርመው ስትሞክር ምክርህን ቢቃወምህ ጓደኝነትህን ወደ ጠላትነት አትቀይር። ቢያንስ ስህተቱን እንዳይጨምር ተስፋ በማድረግ ለሱ አዛኝ እንደሆንክ ቀጥል።

"ከመጥፎም የባሰ መጥፎ አለ" ይባላል። ሰዎችን በደግነት ከቀረብካቸው ትንሹም ሆነ ትልቁ ስህተታቸው ሊያስቆጣህም። በደስታ ትኖራለህ። አዒሻ (ረ.ዐ) ስትናገር "ነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) በግል ጉዳያቸው የበደላቸውን ሰው ለመበቀል አስበው አያውቁም። ሴትንም ሆነ አገልጋይን በእጃቸው መትተው አያውቁም። በአላህ መንገድ ላይ ሲዋጉ ካልሆነ በቀር። እሳቸውን በግል የበደሏቸውን ሰዎች ተበቅለው አያውቁም። የአላህ ትዕዛዝ ሲጣስ ካላዩ በስተቀር" ብላለች። (ሙስሊም)

ነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) ይቆጡ እንደነበር ጥርጥር የለውም። ሆኖም ቁጣቸው ለአላህ ነበር። ሰራሳቸው ሲሉ አይቆጡም። የሁለቱን ልዩነት መረዳት ይቻል ዘንድ ቁጣዩን ምሳሌ እንመልከት። ትንሹ ልጅህ አንድ ቀን ጠዋት ላይ መጥቶ ለትምህርት ቤት ሁለት ብር ስጠኝ ብሎህ ቦርሳህን ስትከፍት ሙቶ ሙቶ ብር ብቻ ነው ያለህ። ይህ መቶ ብር ነው ዘርዝረህ ሁለት ብር ብቻ ውሰድና ሌላውን መልስ ብለህ ሰጠኸው። መልሱን ይዞ እንዲመጣ ደጋግመህ አሳሰብከው። ከአስር በኋላ ወደ ቤት ሲመለስ ሁሉንም ብር አጥፍቶ መጣ። ምን ታደርጋለህ? ምን ያህል ትናደዳለህ? ልትመታው ትችላለህ። ከዚህ በኋላ ሳንቲም የሚባል ላትሰጠው ልትወስን ትችላለህ።

በሌላ ቀን ከአስር በኋላ ወደ ቤት ስትመጣ የአስርን ሶላት መስገዱን ትቶ ጌም ሲጫወት ደረስክ። ባለፈው የተናደድከውን ያህል ነው አሁን የምትናደደው? የመጀመሪያው ቁጣህ የጠነከረ እንደሚሆን አስባለሁ። የአላህ መልዕክተኛ ቁጣ ግን

ለአላህ ብቻ ነበር። በተደጋጋሚ ሰዎችን ይመከራሉ። የማይቀበሏቸው ከሆነ አይጋተሩም። ምክንያቱም ቅናቻ ያለው በአላህ (ሱ.ወ) እጅ ላይ ብቻ ነው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተቡከ ደርሰዋል። ሶሪያ ድንበር። ከሮማውያን ኢምፓየር አጠገብ። ለደህያ አል ከልቢ ደብዳቤ አስይዘው ወደ ቀይሰር ላኩት። ቀይሰር ደብዳቤውን አንብቦ እንደጨረሰ ቀሳውስቶችንና የንጉሳዊ ቤተሰብ አባላትን ጠራና በሩን ዘግቶ "እንደምታውቁት ይህ ሰው መጥቷል። ከቀጣዮቹ ሶስት ነጥቦች በአንዱ እንድስማማም ጠይቆኛል" አላቸው።

1. ኃይማኖቱን እንድቀበል

2. መሬት እንድንሰጠውና የመሬቱ የባለቤትነት ሙበት ግን የኛው እንደሆነ

3. ከሱ ጋር ጦርነት እንድገጥም።

ከዚያም ቀይሰር "ወላሂ መጽሐፍቶቻችሁን ስታነቡ እንደምታውቁት በርግጠኝነት መሬታችንን ይወስደዋል። ታዲያ ለምን ኃይማኖቱን አንቀበልም ወይም ደግሞ ንብረት እንሰጠውና መሬታችንን እናድን" አላቸው።

ቀሳውስቱ ኃይማኖታችሁን ቀይሩ እንዳላቸው ሲረዱ በቁጣ ጮሁ። የለበሷቸውን ጋወኖች ወለቁ። ከቁጣቸውና ከመወራጨታቸው የተነሳ ካባቸው ከላያቸው ላይ ወደቀ።

"ከርስትናን እንድንተው ወይም ከሂጃዝ የመጡ ገጠሬዎች ባሪያ እንድንሆን ነው እየጠየቅከን ያለኸው?" አሉት። ቀይሰር ደነገጠ። ይህን አስተያየት በመስጠቱ ራሱን ችግር ውስጥ እንደከተተ ተረዳ። እነዚህ ቀሳውስት በህዝቡ ዘንድ ትልቅ ተቀባይነት ያላቸው ሰዎች ናቸው። ስለዚህ በዚህ ሁኔታ ከወጡ መላውን የሮማ ግዛት በሱ ላይ እንዳያሳምጹበት ፈራ። ለማረጋጋት በማሰብም ይህን "ጥያቄ የጠየቅኳችሁ በእምነታችሁ ላይ ያላችሁን ጥንካሬ ለመፈተሽ ስል ነው" አላቸው። ቀይሰር ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) እየሱስ እንደሚመጡ የተናገረላቸው ነቢይ መሆናቸውን አውቋል። ነገር ግን ግምቱን ሊያረጋግጥ ፈለገ። ታጂብ ከሚባሉ የአረብ ጎሳዎች ውስጥ አንድ ሰው አስጠራ። የከርስትና ኃይማኖት ተከታይ አረቦች ናቸው።

"ከናንተ መካከል አረብኛ አቀላጥፎ መናገር የሚችልና ቃላቶችን በደንብ የሚያስታውስ ሰው ፈልግና ሙሐመድ ለላከልኝ ደብዳቤ መልስ ይዞ ይሂድ" አለው። ከታጂብ ጎሳ አባል የሆነው ይህ ሰው በኑ ተኑኽ ከሚባለው ጎሳ አንድ ሰው አመጣለሁ አለ። በኑ ተኑኽም ከርስቲያን አረቦች ናቸው። ሄራከለስ ደብዳቤውን ለሰውዬው እየሰጠ እንዲህ አለው፡- ይህን ደብዳቤ ለዚህ ሰው ስጥልኝ። ስታናግረው ቀጣዮቹን ሶስት ነገሮች በደንብ ተመልከት አለው።

1. ለኔ የፃፈውን ደብዳቤ ይጠቅሳል?

2. የእኔን የመልስ ደብዳቤ ሲያነብ ምሽትን ይጠቅሳል?

3. ጀርባው ላይ ለየት ያለ ነገር አለው?

አልተኑኪ ሶሪያን ለቆ ተቡክ ሲደርስ ኑብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከባልደረቦቻቸው ጋር መሬት ላይ ቁጭ ብለው አገኛቸው። አልተኑኪ መጣና

"ባልደረባችሁ የታለ?" በማለት ጠየቃቸው።

"ይሄው" አሉት። ከፊት ለፊታቸው ቁጭ አለና ደብዳቤውን ሰጣቸው። ኑብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተቀበሉና ጭናቸው ላይ አስቀመጡት። ከዚያም "ከየት ነው የመጣኸው?" በማለት ጠየቁት። ሰውዬውም "እኔ የተኑኽ ወንድም ነኝ" አላቸው። ኑብዩም "መስለም ትፈልጋለህ? አሃዳዊውን እምነት መከተል ትሻለህ? የአባትህን የኢብራሂምን እምነት" አሉት። ኑብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይህ ሰው እንዲሰልም በጣም ጓጉተው ነበር።

በእርግጥም ይህን የተኑኽ ሰው ከመስለም የሚከለክለው ምንም ነገር አልነበረም። ለህዝቡ ኃይማኖት ካለው ጉጉት በስተቀር። አልተኑኽ በተረጋጋ ድምጽ "እኔ የህዝቤ ኃይማኖት ያለኝ ከህዝቤ የመጣሁ መልዕክት አድራሽ ነኝ" አላቸው። ኑብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተናደው በሱ ላይ ችግር ለመፍጠር አልሞከሩም። ሳቁና እንዲህ አሉ፡
- "የምትወዳቸውን ሰዎች ወደ ሀቁ ጎዳና መምራት አትችልም። አላህ ብቻ ነው የፈለገውን ሰው መምራት የሚችለው። የሚመሩትን ሰዎች በእርግጠኝነት የሚያውቀውም እሱ ብቻ ነው" አሉ። ከዚያም በተረጋጋ ድምጽ "የተኑኽ ወንድማችን ሆይ!

ለኪሰራ ደብዳቤ ላኩለት። ቀደደው። አላህ እሱንና ግዛቱን ይቀዳድዋል። ለነጁሰ ደብዳቤ ላኩኝ። ኢቃጠለው። አላህ ግዛቱን ያቃጥልለታል። አንተን ለላከህ ሰው ደብዳቤ ላኩኝ። አስቀመጠው። በህይወት ላይ ጥሩ ነገር እስካለ ድረስ ሰዎች በሱ ላይ ችግር መፍጠራቸውን ይቀጥላሉ።" አልተኑኪ የቀይሰርን ጥያቄዎች ማስታወስ ጀመረና ለራሱ "ይህ እንድይዝ ካሳሰበኝ ሶስት ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው" አለ። እንዳይረሳው ፈራና ፃፈው። ኑብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከጎናቸው ለተቀመጠው ሰው ደብዳቤውን ሰጡት። አልተኑኪም "ከመካከላችሁ መፃፍና ማንበብ የሚችል ሰው ማን ነው?" ሲል ጠየቀ። "ሙአዊያ" አሉት።

ሙአዊያ ደብዳቤውን ማንበብ ጀመረ። እንዲህ ይላል፡- "ለአማኞች ለተዘጋጀውና እንደ ሰማያትና ምድር ሰፊ ወደ ሆነው ጀነት ጠራኽኝ። ታዲያ ገሃነም

እሳት የት ነው ያለው?" ነብዩም "ሱብሃነላህ ቀኑ ሲመጣ ምሽቱ የታለ?" አሉ። አልተኑኺ ቀይሰር ያዝ ያለው ሁለተኛ ነገር ይህ እንደሆነ አሰበ። ማስታወሻ ያዘ። ሙአዊያ ደብዳቤውን አንብቦ ሲጨርስ ነብዩ በትህትና "አንተ መልዕክት አድራሽ ነህና መብቶች አሉህ። እዚህ በሰጠታ መልክ ብሰጥህ ልትወስደው የምትፈልገው ነገር ቢኖር እንሰጥህ ነበር። ነገር ግን እኛ አሸዋ ላይ የተቀመጥን መንገደኞች ነን" አሉት ለአልተኑኺ። ማለትም ስጦታ ብሰጥህ ደስ ይለኝ ነበር። ነገር ግን እንደምታየው በአሸዋ ላይ የተቀመጥን መንገደኞች ነን፤ ምንም የለንም።

ኡስማን (ረ.ዐ) ተነሳና "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እኔ የሆነ ነገር እሰጠዋለሁ" አለና ጀለብያና ፎጣ አምጥቶ አልተኑኪ ጭን ላይ አስቀመጠለት።

ከዚያም ድንቁ ነብይ "ይህን ሰው የሚወስደው ማን ነው?" ሲሉ ጠየቁ። ማን ነው የሚያስተናግደው ማለታቸው ነው።

"እኔ አስተናግደዋለሁ" አለ አንድ አንሷር። አንሷሩና አልተኑኺ ጉዞ ጀመሩ። አልተኑኺ ቀይሰር የጠየቀውን ሶስተኛ ነገር አስታወሰ። በነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) ጀርባ ላይ ማህተም ስለመኖሩ። ጥቂት እርምጃዎችን እንደተራመደ በድንገት "የተኑኽ ወንድማችን አንዴ ና" አሉት ነብዩ (ሲ.ዐ.ወ)። ፈጠን ፈጠን እያለ መጣና አጠገባቸው ቆመ። ልብሳቸውን ገልጠው ጀርባቸውን እያሳዩት "ይሄውልህ ማስታወሻ ያዝ የተባልከውን ነገር ያዝ" አሉት። አልተኑኺም "ጀርባውን ስመለከት በትከሻዎቹ መካከል ትልቅ ማህተም አየሁ" ሲል ተናግሯል።

አንድ አስተሳሰብ...

ዓላማው ሰዎች ስህተቶቻቸውን እንዲገነዘቡ ማድረግ ነው። አንተ ባለህበት ስህተታቸውን ማረማቸው የግድ ላይሆን ይችላል። ስለዚህ አትጨነቅ።



ላመናጨቀህ ሰው በትህትና መልስለት

በጣም በተለመደ ሁኔታ ሰዎች የሚቀርቡህ እነሱ ሊቀርቡህ በሚፈልጉት መልኩ እንጂ አንተ በምትፈልገው መልኩ አይደለም። በፈገግታ የቀረብከው ሰው ሁሉ በፈገግታ አይቀርብህም። እንደውም አንዳንዱ መጥፎ ነገር በማሰብ ተበሳጭቶ "ምን ያስቅሃል?" ሊልህ ይችላል። ስጦታ የሰጠኸው ሰው ሁሉ ውለታህን አይመልስልህም። እንደውም ስጦታ ያበረከትከላቸው ሰዎች ተሰባስበው ሞኝና አባካኝ ሰው ነው እያሉ ሲያሙህ ልትሰማ ትችላለህ። በጥሩ ሁኔታ ያናገርከውና ያሞገስከው ሰው ሁሉ ተመሳሳይ ምላሽ አይሰጥህም። አላህ ለሰዎች የተሊያዬ ሲሳይ እንደሰጣቸው ሁሉ የተሊያዬ ባህሪ ሰጥቷቸዋል። መለኮታዊው አስተምህሮ ሰዎችን እንዴት መቅረብ እንዳለብን እንዲህ ሲል ያስተምረናል።

"መልካሚቱና /ከፉይቱም/ ፀባይ አይስተካከሉም። በዚያች መልካም በሆነችው ፀባይ መጥፎይቱን ገፍትር። ያን ጊዜ ያ ባንተና በሱ መካከል ጠብ ያለው ሰው እሱ ልክ እንደ አዛኝ ዘመድ ይሆናል።" አንዳንድ ሰዎች ችግራቸው መፍትሄ የለውም። እነሱን መቀየርም አይቻልም። የዚህ ዓይነት ሰዎችን መቅረብ ያለብህ እነሱ በሚፈልጉት መልኩ ስትጓዝ ብቻ ነው። ታግሰህ ከነሱ ጋር ተቆያለህ። አሊያ ትተሃቸው ትሄዳለህ።

በአንድ ወቅት አንድ ሰው ከአንድ ነጋዴ ጋር ይጓዛል። ይህ ሰው በጉዞ ላይ የሚያስፈልጉ ሰራዎችን በሙሉ ይሰራል። ምግብ በማዘጋጀት የጉዞ ጓደኛውን ይመግባል። ጭነቱን ያወርዳል። ግመሎቹን ይመግባል። እስኪደክመው ድረስ። እየተመለሱ እያለ ምግባቸውን ለማብሰል አንድ ቦታ ላይ አረፉ። አንደኛው እግሩን ዘርግቶ ተኛ። ሌላኛው ጭነቱን አወረደ። ለጓደኛውም "እኔ ስጋ እስከቆራርጥ ተነሳና እንጨት ሰብስብ አለው። "ወላሂ ለረጂም ሰዓት መጓዙ በጣም አድክሞኛል" አለው። ራሱ እንጨቱን ሰበሰበና "እሽ እሳቱን አቀጣጥል?" ሲል ጠየቀው። "ወደ እሳት ስቀርብ ጭሱ ያፍነኛል" አለ። ራሱ አቀጣጠለ። "ስጋውን በመቁረጥ አግዘኝ?" ሲል ጠየቀው። "እጄን ቢላዋ ሊቆርጠኝ ስለሚችል ይቅርብኝ" አለው። ራሱ ቆራረጠ። "እሺ ስጋውን መጥበሻው ላይ አድርገህ አብስል?" ሲል ጠየቀው። "ምግቡ እስኪበስል ድረስ ቁጭ ብሎ መጠበቅ በጣም አድካሚ ነገር ነው" አለው። ራሱ

አበሰለ። ምግቡን ካበሰለ በኋላ በጣም ስለደከመው ጋደም አለና "ሱፍራውን አንጥፍና ምግቡን በሳህን አድርገህ አቅርብ?" ሲል ጠየቀው።

"እኔ በጣም ደክሞኛል። አሁን ይህን የምሰራበት ምንም አቅም የለኝም" አለው። ተነሳና ምግቡን አቀረበ። "ተነስተህ መብላት ትችላለህ?" ብሎ ሲጠይቀው "ወላሂ ሁሉንም ነገር እምቢ ማለት በጣም አሳፈረኝ። እስቲ አሁን አንኳን እሺ ልበልህ" አለና ተነስቶ መብላት ጀመረ።

የዚህ ዓይነት በርካታ ሰዎች ሊገጥሙህ ይችላል። በዚህ በጣም አትዘን። ይልቁንም እንደ ተራራ ጠንካራ ሁን። አርኢያችንና አስተማሪያችን ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በስሜት ሳይሆን በምክንያት ነበር ሰዎችን የሚቀርቡት። የሰዎችን ስህተት አያጎሉም። በጥበብ ይቀርቧቸዋል። አንዴ ከባልደረቦቻቸው ጋር ተቀምጠው ሳለ አንድ ቤድዊን መጣና የደም ካሳ መክፈል ስለተቸገረ እርዳታ እንዲሰጡት ጠየቃቸው። ይህ ሰው ራሱ ወይም አንዱ ቤተሰቡ ሰው ገድሏል። ስለዚህ ለተጎጂው ቤተሰብ የደም ካሳ መክፈል ይችል ዘንድ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) በገንዘብ እንዲረዱት ፈልጓል። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተወሰነ ነገር ሰጡትና "ላንተ ጥሩ ሆንኩልህ?" ሲሉ በትህትና ጠየቁት።

"አንተ ጥሩም ትሁትም አይደለህም" አላቸው።

ይህን የሰሙት ሶሃቦች ተናደዱና ሊመቱት ተነሱ። ነገር ግን ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከለከሏቸው።

ወደ ቤቱ ሄደው ጠሩትና "ወደኛ መጥተህ እርዳታ ጠየቅከን። ረዳንህ። የተናገርከውን ተናገርክ" አሉና ተጨማሪ ነገር ሰጡት። "ላንተ ጥሩ ሆንኩልህ?" አሉት። ገጠሬውም "አዎ አላህ በቤተሰብዎና በዘመድ አዝማድዎ ምንዳ ይስጥዎት" አላቸው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰውዬው መደሰቱን ሲያውቁ ደስ አላቸው። ሆኖም ባልደረቦቻቸው አሁንም ለሰውዬው ጥላቻ ሊኖራቸው ይችላል ወይም አንዱ ባልደረባቸው ይህንን ሰው መንገድ ላይ ቢያገኘው ጥላቻውን ሊገልጽ ይችላል ብለው ፈሩ። ስለዚህ ይህን ስሜት ከልባቸው ውስጥ ማውጣት ፈለጉ። እናም ለሰውዬው፡- "ወደኛ መጥተህ እርዳታ ጠየቅከን። ሰጠንህ። ነገር ግን የተናገርከውን ተናገርክ። በዚህም ምክንያት ባልደረቦቼ ተበሳጭተውብሃል። ወደነሱ ሄደን አሁን ያልከኝን ነገር ብትላቸው ይህ ስሜት ከልባቸው ሊወጣ ይችላል" አሉት። ይዘውት ሄዱና "ይሄ ወንድማችን ወደኛ መጥቶ እርዳታ በጠየቀን ጊዜ ሰጠነው። ሆኖም የተናገረውን ነገር ተናገረ። እንደገና ጠርተን ጨምረን ስንሰጠው መደሰቱን ገልጿል። አይደለም እንዴ? እከሌ" አሉት። እሱም "አዎ! አላህ በቤተሰብዎና በዘመድ አዝማድዎ ይመንዳዎት" አለ። ወደ ቤቱ ለመሄድ ሲነሳ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለባልደረቦቻቸው የሰዎችን ልብ እንዴት ማሸነፍ እንደሚቻል ትምህርት ሊሰጧቸው ፈለጉ። እናም "የእኔና የዚህ ሰው ምሳሌ ግመሉ እንዳመለጠችው ሰው ነው።

የተወለኑ ሰዎች ከኋላ ሲከተሏት ግመሏ ደንብራ ሮጠች። የባሰውኑ ርቃ ሄደች። ከዚያም የግመሏ ባለቤት "እባካችሁ ግመሏን ለኔ ተውልኝ። እኔ ባህሪዋንና ምን እንደምትፈልግ አውቃለሁ" አለና መሬት ላይ የወዳደቁ ቴምሮችን በመሰብሰብ አጠገቡ እስክትመጣ ድረስ ጠራት። ከዚያም ኮርቻውን አስሮ ጋለባት። ያንን ነገር ስታደርጉ ዝም ብላችሁ ኖሮ ይህ ሰው ጀህነም እሳት ይገባ ነበር። ማለትም እንዲርቅ ብታደርጉት ኖሮ ይህን ኃይማኖት ትቶ ጀሃነም እሳት ይገባ ነበር። (አልበዘር)

ማስተዋል አንድን ድርጊት ያሳምረዋል። ሸካራነት ያበላሸዋል። "መልካሚቱና / ከፉይቱም/ ፀባይ አይስተካከሉም። በዚያች መልካም በሆነችው ፀባይ /መጥፎይቱን/ ገፍትር። ያን ጊዜ ያ ባንተና በሱ መካከል ጠብ ያለው ሰው እሱ ልክ እንደ አዛኝ ዘመድ ይሆናል።" ነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) መካን በያዙ ጊዜ በካዕባ ዙሪያ ጠዋፍ እያደረጉ ነበር። ሙስሊም ነኝ ብሎ የሚዋሽ ፋደላህ ቢን ኡመይር የሚባል ሰው ከጀርባቸው ጠዋፍ ያደርጋል። እሳቸውን ለመግደል ሁኔታዎችን እያመቻቸ ነበር። ነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) ይህንን ነገር አወቁ። ዞር አሉና "አንተ ፈዷላህ ነህ?" አሉት።

"እዎ ነኝ የአላህ መልዕከተኛ!" አላቸው።

"ምን ልታደርግ አስበሃል?" አሉት። "ምንም! አላህን እያስታወስኩ ነው" አላቸው።

ነብዩም ሳቅ አሉና "የአላህን ምህረት እከጅላለሁ" አሉ። ፈዷላህ ኋላ ላይ ስለዚህ ክስተት ሲያወራ የአላህ መልዕከተኛ እጃቸውን ደረቴ ላይ ሲያስቀምጡ ልቤ ተረጋጋ። ወላሂ እጃቸውን ነከልቤ ላይ ሳያነሱ አላህ ለሳቸው ጠንካራ ፍቅርን ልቤ ውስጥ አስገባ።

ፈዷላህ ወደ ቤቱ በመሄድ ላይ ሳለ መንገድ ላይ አንዲት ወዳጁን አገኛት። ስታዬው "ና እናውራ" አለችው። "አይሆንም" በማለት መለሰ። በድጋሚ "ና እናውራ" አለችው። "አይሆንም። አላህና ኢስላም ይህን ይከለክሉሻል። ሙሐመድና ቡድኑ ሲያሸንፉና ጣኢታት ሲሰባበሩ ብታይ ኖሮ የአላህ ኃይማኖት እንደሚበልጥ ሸርከ በጨለማ እንደሚዋጥ ትመሰክሪ ነበር" አላት። በዚህ መልኩ ፈዷላህ ከደጋግ ሙስሊሞች አንዱ ለመሆን በቃ።

ነብዩ (ሲ.ዐ.ወ) ለሰዎች ምህረት በማድረግ ልባቸውን ያሸንፉ ነበር። ሰዎችን ለመቀየርና እነሱን ወደ ጥሩ ነገር ለማምጣት የሚያደርሱባቸውን መጥፎ ድርጊቶች ይቋቋሙ ነበር።

አቡ ጣሊብ ነብዩን (ሲ.ዐ.ወ) ከቁረይሾች ጉዳት በተደጋጋሚ ይጠብቋቸው

ነበር። እሳቸው ከሞቱ በኋላ ግን ቁረይሾች በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ የሚያሳድሩትን ጫና ጨመሩ። አጎታቸው በህይወት እያሉ ያልደረሰባቸው ጉዳት ከሞቱ በኋላ ይደርስባቸው ጀመር። ነብዩ ሌላ መጠጊያና ድጋፍ የሚያገኙበትን መንገድ ማሰብ ጀመሩ። በመሆኑም የሰቂፍን ጎሳ ድጋፍ ለማግኘት ሲሉ ወደ ጣኢፍ ሄዱ። የሰቂፍ ጎሳ መሪ የሆኑ ሶስት የተከበሩ ሰዎችን ለማናገር ሞከሩ። ሶስት ወንድማማቾች ናቸው። አብድ ጀሊል ቢን አምር እና ወንድሞቹ መስኡድና ሀቢብ።

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከነሱ ጋር ቁጭ አሉና ወደ አላህ ጠሯቸው። በኢስላም መንገድ ላይ እንዲያግዟቸውና የራሳቸው ህዝቦች ከሚያደርሱባቸው ተቃውሞ ከጎናቸው እንዲቆሙ ጠየቋቸው። ሆኖም መልሳቸው አሳፋሪ ነበር። አንደኛው "አላህ አንተን በትክክል ልኮህ ከሆነ የካዕባን ሽፋን እቀደዋለሁ" አለ። ሌላው ደግሞ "አላህ ሌላ የሚልከው ሰው አጥቶ ነው እንዴ አንተን የሚልከው?" ሲል አሾፈ። ሶስተኛው የሚሰጠው ምላሽ ምን ዓይነት መሆን እንዳለበት አሰበ። የሚጠቀማቸው ቃላት ከወንድሞቹ ይበልጥ ተንኮል አዘል እንዲሆኑ ፈልጓል። "ወላሂ ላንተ ምንም ዓይነት መልስ መስጠት አልፈልግም። እንደምትለው የአላህ መልዕክተኛ ከሆንክ መልስ ለመስጠት በጣም አደገኛ ሰው ነህ። በአላህ ላይ የምትዋሽ ከሆነ ደግሞ በጭራሽ አላናግርህም!" አላቸው።

ነብዩ ከሰቂፍ ውስጥ ታላላቅ የሚባሉት ሰዎች በሰጧቸው ምላሽ በጣም አዝነው ለመሄድ ተነሱ። ቁረይሾች ሰቂፎች እንደተቃወሟቸው ካወቁ የበለጠ ጉዳት እንዳያደርሱባቸው ፈሩ። ስለሆነም "እባካችሁ ይህን ውይይት በሚስጥር ያዙት" አሏቸው። ነገር ግን አላደረጉትም። ይባስ ብለው ልጆችንና ሞኞችን በማነሳሳት እየተከተሉ ይሰድቧቸውና ድንጋይ ይወረውሩባቸው ጀመር። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ራሳቸውን ለማዳን ፈጠን ፈጠን እያሉ ይራመዳሉ። የተከበረው እግራቸው በብዛት ይደማ ጀመር። በመካከለኛ ዕድሜ ላይ ነበሩ። ከአርባ ዓመት በላይ ሆኗቸዋል። ከነሱ ከራቁ በኋላ የተምር ዛፍ ጥላ አገኙና እዚያ ላይ አረፍ አሉ። በዚህ ወቅት የሚያስቡት ቁረይሾች ምን ሊያደርጓቸው እንደሚችሉ ነበር። መካ እንዴት ብለው ይግቡ? ወደ ሰማይ እየተመለከቱ "አላህ ሆይ! የአቅሜን ደካማነት፣ የብልሀቴን ጥቂትነት ከሰዎች ዘንድም የተናቅኩ መሆኔን ለአንተ ስሞታ አቀርባለሁ። የአዛኞች ሁሉ አዛኝ የሆንከው የደካሞች አምላክ ሆይ! ለማን ትተወኛለህ? ለሚጠሉኝ ባእዶች? ጉዳዩን ከጠላት እጅ አስገባኸውን? አንተ ካልተቆጣህብኝ ግድ የለኝም። ማርታህና ይቅርታህ ይበልጥብኛል። ቁጣህ እንዳይሰፍንብኝ ጨለማን በገሰሰከበት ብሩህ ማንነትህ፣ ይህቺንም ሆነ መጪውን ዓለም ባቆምክበት ሀይልህና ችሎታህ እጠይቅሀለሁ። ውዴታህን እስካገኝ እደከማለሁ። መላም ሆነ ሀይል ባንተ ቢሆን እንጂ የለም።" በዚህ ሁኔታ ቁጭ ብለው እያለ ደመና መጣና ከበባቸው። ወደ ሰማይ ሲመለከቱ ጅብሪል መጣ። ጅብሪል ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) "ሙሐመድ ሆይ! አላህ ምን እንዳሉህና ምን እንዳደረጉህ ሰምቷል። የተራሮች መልአክ እንዲታዘዝህ

ልኮልሃል። የምትፈልገውን ነገር እዘዘው" አላቸው። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) አንድ ቃል ከመናገራቸው በፊት የተራሮች መልአክ እንዲህ አላቸው፡- "የአላህ ሰላም ባንተ ላይ ይሁን። የአላህ መልዕክተኛ ሙሐመድ ሆይ! አላህ ሰዎቹ ያሉትን ነገር ሰምቷል። እኔ የተራሮች መልአክ ነኝ። ጌታህ ወዳንተ ልኮኛል። ስለዚህ የፈለግከውን ነገር እዘዘኝ" አላቸው።

አሁንም አንድ ቃል ከመተንፈሳቸው በፊት የተራሮች መልአክ እንዲህ በማለት ሃሳብ ያቀርብላቸው ጀመር።

"ከፈለግክ በሁለቱ ተራሮች መካከል አጣብቃቸዋለሁ" አለ በመካ ግራና ቀኝ ያሉ ሁለት ተራሮችን እያመለከተ። የተራሮች መልአክ ትዕዛዝ ይጠብቅ ጀመር። "ይልቁንም" አሉ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) የራሳቸውን ፍላጎትና የበቀል ስሜት በመግታት "ይልቁንም እታገሳቸዋለሁ። ምክንያቱም አላህ ከነሱ ውስጥ አሱን በብቸኝነት የሚያመልኩ ሰዎችን ሊያስነሳ ይችላል" አሉ።

ጀግና ሁን...

በእኔና በወንድሞቼ መካከል ያለው ግንኙነት በእርግጥም የአጎቶቼ ልጆች ችግር አለባቸው። ሲጋዬን ሲበሉት የነሱን እተዋለሁ። ከብሬን ሲያዋርዱት የነሱን እገነባለሁ። እኔን ለመርዳት አይቸኩሉም። እኔን ለዕርዳታ ሲጠሩኝ ግን ፈጥኜ እደርሳለሁ። ቂም አልይዝባቸውም። መሪ ቂም አይዝምና።